የፍልስፍና እይታ

ክፍል 1

የፍልስፍና እይታ በክፍል 1 ሚዳሰሱት አርእስት

1, የፍልስፍና ትርጉም እና ምንነት

2, ፍልስፍና እና መጽሐፍ ቅዱስ

3,ፍልስፍና እና ቅዱስ ቁርአን

4,ያልተጠኑ የኢትዮጵያውያን ፍልስፍና

ይሔ ፅሑፍ የተፃፈበት ዋናው ምክንያት በሀገራችን ሙሉ በሙሉ ማለት ባይቻልም ግን አብዛኞች ኢትዬጵያውያን ፍልስፍናን ከእውነተኛው ትርጓሜ ጋር ሳይሆን ከተለመደው ትርጉም ጋር በፍጥነት ሲያገናኙት ይስተዋላል ስለዚህ ይህን አስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ሊያስተካክል ባይችልም በከፊል ለማስተካከል የተፃፈ ፅሑፍ ነው።

1,የፍልስፍና ትርጉም እና ምንነት

ፍልስፍና የሚለው ቃል ከግሪኩ ታPhilos» /ፊሎስ/ ማለትም ፍቅር እና፣

« sophos» /ሶፎስ/ (ጥበብ) የተገኘ ውሁድ ነው። በቀጥታው የጥበብ ፍቅር

ወይም ፍቅረ ጥበብ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

በመሆኑም ጥበብ እና ፍቅርን መውደድ የፍልስፍና መሰረታዊ ትርጉም ነው።

ፍልስፍና በአንዳንድ ሰዎች አገላለፅ ፍልስፍና የአንድን ነገር ምንነት ለመረዳት በጥያቄ የሚጀምርና በማሰላሰል ውስጥ ትክክለኛ መረዳትን ለማግኘት የሚደረግ የሀሳብ መመላለስ ነው።

በመሆኑም ፍልስፍና

እውቀትን፣ እውነትን፣ ጥበብን መውደድ፣ መሻት፣ መመርመር ተብሎ ሊተረጎም

ይችላል። ባንድ በኩል ወደ ጥበብ የተሳበ፣ ጥበብን የወደደ እንደዚሁም

የጥበብ ባለሟልን የሚያመለክት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ጥበብን ወዶ

ሌላውም እንዲወድ ምክንያት የሚሆን ለማለት ይውላል።

2,ፍልስፍና እና መጽሐፍ ቅዱስ

ከላይ እንደተመለከትነው"ፍልስፍና" የሚለው ቃል ጥሬ ፍቺ ጥበብንና ፍቅርን መዉደድና መከተል ከሆነ ስለ ጥበብና ፍቅር እንደሚል እንመለከታለን

1,ስለ ጥበብ

"፤ ጥበብን አግኝ፤ ማስተዋልን አግኝ፤ አትርሳም፥ ከአፌም ቃል ፈቀቅ አትበል። "

(መጽሐፈ ምሳሌ 4: 5)

"፤ ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።

(የሉቃስ ወንጌል 2: 52)

"፤ ሙሴም የግብፆችን ጥበብ ሁሉ ተማረ፥ በቃሉና በሥራውም የበረታ ሆነ። "

(የሐዋርያት ሥራ 7: 22)

"፤ እኔም ብርሃን ከጨለማ እንደሚበልጥ እንዲሁ ጥበብ ከስንፍና እንዲበልጥ አየሁ። "

(መጽሐፈ መክብብ 2: 13)

"፤ በታላቅ ጥበብህና በንግድህ ብልጥግናህን አብዝተሃል በብልጥግናህም ልብህ ኰርቶአል። "

(ትንቢተ ሕዝቅኤል 28: 5)

"፤ ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም። "

(የሐዋርያት ሥራ 6: 10)

"፤ እግዚአብሔርም ለሰሎሞን እጅግ ብዙ ጥበብና ማስተዋል በባሕርም ዳር እንዳለ አሸዋ የልብ ስፋት ሰጠው። "

(መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 4: 29)

"፤ ገመዳቸው የተነቀለ አይደለምን? አለጥበብም ይሞታሉ።

"

(መጽሐፈ ኢዮብ 4: 21)

"፤ የጻድቅ አፍ ጥበብን ያስተምራል፥ አንደበቱም ፍርድን ይናገራል። "

(መዝሙረ ዳዊት 37: 30)

"፤ የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደ ሆነ ቍጠሩ። እንዲህም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፥ በመልእክቱም ሁሉ ደግሞ እንደ ነገረ ስለዚህ ነገር ተናገረ። "

(2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3: 15)

"፤ በገና የሚመቱና የሚዘምሩም ድምፅ እንቢልታንና መለከትንም የሚነፉ ድምፅ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፥ የእጅ ጥበብም ሁሉ አንድ ብልሃተኛ እንኳ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይገኝም፥ የወፍጮ ድምጽም ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፥ "

(የዮሐንስ ራእይ 18: 22)

"፤ ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል። "

(የያዕቆብ መልእክት 1: 5)

"፤ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። "

(2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 3: 15)

"፤ ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤ "

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 3: 10)

2,ስለ ፍቅር

"፤ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመስጠት ይልቅ ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም። "

(የዮሐንስ ወንጌል 15: 13)

"፤ ወንድምህንም በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆንህ እንግዲህ በፍቅር አልተመላለስህም። ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተለትን እርሱን በመብልህ አታጥፋው። "

(ወደ ሮሜ ሰዎች 14: 15)

"፤ ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ። "

(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 14: 1)

"፤ የጐመን ወጥ በፍቅር መብላት የሰባ ፍሪዳን ጥል ባለበት ዘንድ ከመብላት ይሻላል። "

(መጽሐፈ ምሳሌ 15: 17)

"፤ ወደ ወይን ጠጁም ቤት አገባኝ፥ በእኔ ላይ ያለው ዓላማውም ፍቅር ነው። "

(መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 2: 4)

"፤ በሰው ገመድ በፍቅርም እስራት ሳብኋቸው፤ ለእነርሱም ቀምበርን ከጫንቃቸው ላይ እንደሚያነሣ ሆንሁ፥ ድርቆሽም ጣልሁላቸው። "

(ትንቢተ ሆሴዕ 11: 4)

"፤ ወንድሜ ዮናታን ሆይ፥ እኔ ስለ አንተ እጨነቃለሁ፤ በእኔ ዘንድ ውድህ እጅግ የተለየ ነበረ፤ ከሴት ፍቅር ይልቅ ፍቅርህ ለእኔ ግሩም ነበረ። "

(መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 1: 26)

"፤ ጻድቃንና ጠቢባን ሥራዎቻቸውም በእግዚአብሔር እጅ እንደ ሆኑ፥ ይህን ሁሉ እመረምር ዘንድ በልቤ አኖርሁ፤ ፍቅር ወይም ጥል ቢሆን ሰው አያውቅም ሁሉ ወደ ፊታቸው ነው። "

(መጽሐፈ መክብብ 9: 1)

"፤ ግልሙትናዋንም ከተመረጡ ከአሦር ሰዎች ሁሉ ጋር አደረገች፥ በፍቅር በተከተለቻቸውም ጣዖቶቻቸው ሁሉ ረከሰች። "

(ትንቢተ ሕዝቅኤል 23: 7)

"፤ ከሰው ክብርን አልቀበልም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ፍቅር በራሳችሁ እንደ ሌላችሁ አውቃችኋለሁ። "

(የዮሐንስ ወንጌል 5: 41-42)

"፤ እግዚአብሔርም ከሩቅ ተገለጠልኝ እንዲህም አለኝ። በዘላለም ፍቅር ወድጄሻለሁ፤ ስለዚህ በቸርነት ሳብሁሽ። "

(ትንቢተ ኤርምያስ 31: 3)

"፤ እንደ ማኅተም በልብህ፥ እንደ ማኅተም በክንድህ አኑረኝ፤ ፍቅር እንደ ሞት የበረታች ናትና፥ ቅንዓትም እንደ ሲኦል የጨከነች ናትና። ፍንጣሪዋ እንደ እሳት ፍንጣሪ፥ እንደ እግዚአብሔር ነበልባል ነው። "

(መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን 8: 6)

"፤ ልቡናውም በያዕቆብ ልጅ በዲና ፍቅር ተነደፈ፥ ብላቴናይቱንም ወደዳት፥ ልብዋንም ደስ በሚያሰኛት ነገር ተናገራት። "

(ኦሪት ዘፍጥረት 34: 3)

"፤ ና፥ እስኪነጋ ድረስ በፍቅር እንርካ፥ በተወደደ መተቃቀፍም ደስ ይበለን። "

(መጽሐፈ ምሳሌ 7: 18)

"፤ በፍቅርም ተናገረው፥ ዙፋኑንም ከእርሱ ጋር በባቢሎን ከነበሩት ነገሥታት ዙፋን

በላይ አደረገለት። "

(መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 25: 28)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ጥበብና ፍቅር በብዙ መልኩ ቢገለጽም በጥቂቱ ይህንን ይመስላል።

ልብ ይበሉ ይህ ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስ ፍልስፍናን የሚፃረር ቃል የለም ማለት አይደለም ለምሳሌ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

፤ እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ። "

(ወደ ቆላስይስ ሰዎች 2: 8)

በአብዛኛው ሰው አረዳድ ይሄ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸው ጥሩ እና አስተማሪ ፍልስፍና እንዳለ ሁሉ መጥፎና ኃላቀር ፍልስፍናም አለ ይሄም ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጸው መጥፎውንና አሳቹን ፍልስፍና ትተን ጥሩውንና አስተማሪውን ፍልስፍና መያዝ አለብን።ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

"፤ ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ "

(1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 5: 20-21)።

3,ፍልስፍና እና ቅዱስ ቁርአን

በቅዱስ ቁርአን ውስጥ ስለ ጥበብ በብዙ ሁኔታና በብዙ መልኩ ተገልጽዋል ከነሱም መካከል ጥቂቶችን እንመለከታለን

ፍልስፍና በኢሥላም ሐኪም ﻴﻢ ﻜ ﺣ ማለት ጥበበኛ ማለት ሲሆን ሓኪም

ﻦ ﻪ ﻜ ﺣ ማለት ደግሞ ፈራጅ ማለት ነው፤ ሁለቱም ሐከመ ﻢ ﻜ ﺣ ﺨﺷ ማለትም

“ፈረደ ተጠበበ ከሚል ግስ የመጡ ናቸው፤ ሒክማህ ﺔ ﻤ ﻜ ﺣ ማለት

“ጥበብ ማለት ሲሆን ሑክም ﻢ ﻜ ﺣ ደግሞ ፍርድ ማለት ነው፤ ጥበብ እና

ፍርድ የጥበበኛው እና የፈራጁ አላህ ባህርያት ናቸው፤ አላህ እጅግ በጣም

ጥበበኛ ነው፡- 28፥9 «ሙሳ ሆይ! እነሆ እኔ አሸናፊው *ጥበበኛው* አላህ ነኝ።

ﺰﻳ ﺰ ﻋ ﻟ ُ ﻪ ّ ﻧ ﺃ َ ﺍ ﷲ َ ﻪ ّ ُ ﻧ ِ ﺇ ٰ ﻯ ﺳ ُ ﻮ ٰ ﻫ ﻳ َ
ُ ﻢ ﻴ ِ ﻜ ﺤ ْ ﺍ ُ 3 ፥6 እርሱ ያ በማሕጸኖች ውስጥ እንደሚሻ

አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነው። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። አሸናፊው

ጥበበኛው ነው። ﺍ ْ ﻟ ﻯ ﻓ ْ ﻢ ُ ﻜ ُ ﺭ ّ ِ ﻮ َ ﺼ ُ ﻳ ﻱ ِ ﺬ ّ ﻟ َ ﺍ ُ ﻮ ﻫ
ﺭ َ ﺤ ْ ﺎ َ ﻣ ِ ﻜ َ ﻴ ْ ﻒ َ ﻴ ﺸ َ ﺀ َ ﺎ ُ ﺷ ﻵ ﺍ ِ ﻟ َ ﻪ ٰ ﺇ ِ ﻟ َ ﺎ ّ ﻫ
ُ ﻢ ﻴ ِ ﻜ َ ﺤ ْ ﺍ ُ ﻮ َ ﺍ ﻟ ْ ﻋ َ ﺰ ِ ﻴ ُ ﺰ

አላህ ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል፤ ጥበብን ከአላህ የተሰጠው ሰው ብዙን

መልካም ነገር በእርግጥ ተሰጥታል፡- 2፥269 *ለሚሻው ሰው ጥበብን

ይሰጣል፤ ጥበብንም የሚሰጠው ሰው ብዙን መልካም ነገር በእርግጥ

ተሰጠ*። የአእምሮዎች ባለቤቶች እንጂ ሌላው አይገሰጽም። ﺤ ْ ﺍ ﻯ ﺗ ْ ُ ﺆ ﻳ
ﻦ َ ﻣ َ ﺔ َ ﻤ ْ ﻜ ِ

ﻳ ﺸ َ ﺀ ُ ﺎ ٓ ﻭ َ ﻣ ﻦ ﻳ ُ ﺆ ْ ﺗ َ ﺍ ﺤ ْ ﻜ ِ ﻤ ْ ﺔ َ ﻓ َ ﻘ َ ﺪ ْ ﺃ ُ ﻭ ﺗ
ِ ﺇ ُ ﺮ ّ ﻛ َ ﺬ ﻳ ﻣ َ ﺎ ﻭ ﷲ ﺇ ً ﺮ ﻴ ﺜ ﻛ ً ﺮ ْ ﻴ ﺧ َ ﻰ

ِ بْ َ بْ لَ ٱْ ٱلَ ْ ٱوُ لْ وُ ٱآّ َ ل

አላህ ጥበብን ለሰው ልጆች በዐቅል እና በነቅል ይሰጣል፤ እነዚህ ሁለት

የጥበብ ጭብጦችን ነጥብ በነጥብ እንይ፦

ነጥብ አንድ ዐቅል ዐቅል ɛƣl ማለት ግንዛቤ Metacognition” ማለት

ሲሆን አላህ በቁርአን ለዐለኩም ተዕቂሉን ِ قْ عَ تَ ْ مُ كّ َ لَ َ عّ ل ኑ ይለናል፦ 12:2

በእርግጥ እኛ *ትገነዘቡ ዘንድ* ዐረብኛ ቁርአን ሲሆን አወረድነው። َ ٱآّ َ زِ إِ ُ ٰه َ نْ لَ نز

ِ قْ عَ تَ ْ مُ كّ َ لَ َ عّ لِ َ ٱ ّ ً يِ بِ رَ بَ ءًا ُ نْ َ ء ُ رْ قُ َ ون ُ 2:242 እንደዚሁ አላህ አንቀጾቹን *ትገነዘቡ ዘንድ*

ለእናንተ ያብራራላችኋል። كَ لِ ُ ٱللَ َ هّ ُ نّ ِ يِ بْ َ يِ كَ لِ ٰ َ ذَ كَ ُ مْ ءْ َ ايِ َ تِ ٰه ِ لَ عَ َ لَ كّ ُ مْ تَ عْ قِ لْ ُ ون َ

“ትገነዘቡ ዘንድ የሚለው ቃላት በአጽንዖትና በእንክሮት ልናጤነው የሚገባ

ሃይለ ቃል ነው፤ የሰው ልጅ አዕምሮ እራሱ ዐቅል ይባላል፤ ዐቅል የጥበብ

ተውህቦ faculty” ነው፤ የሰው ልጅ በተፈጥሮ ጥበብን ይወዳል፤ ፊሎሶፍይ

አፈላ

ተዕቂሉን ون ُ لِ قْ عَ تَ لَ َ فَ أ ይለናል፦ 21:10 *ክብራችሁ በውሥጡ ያለበትን

መጽሐፍ ወደ እናንተ በእርግጥ አወረድን፤ አትገነዘቡምን*? ْ لَ نزَ أْ دَ قَ ل ا ً بْ َ تِ كْ مُ كْ يَ لِ إِ آَ نِ

َ ون ُ لِ قْ عَ تَ لَ َ فَ أ ْ مُ كُ رْ كِ ذِ هِ فِ

“አትገነዘቡምን?” የሚለው ቃላት በአጽንዖትና በእንክሮት ልናጤነው የሚገባ

ሃይለ ቃል ነው፤ ቁርአን ክብራችን በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ነው፤ አዎ

የሰው ልጆች ሊከብሩበት የሚችሉበት ጥበብ ይዟል።

ነጥብ ሁለት ነቅል ነቅል ﺯﻟﻒ ማለት አስተርዮ epiphany” ማለት ሲሆን

“ወሕይ ﻯ ﺣ ﻭ ነው፤ አምላካችን አላህ ወደ ነብያችን ﷺ ”” ጥበብን

አውርዷል፡- 4፥113 አላህም በአንተ ላይ መጽሐፍንና *ጥበብን* አወረደ።

የማታውቀውንም ሁሉ አስተማረህ። የአላህም ችሮታ በአንተ ላይ ታላቅ

ነው።ۚ ﺍﻟ ﻭ ﺑﻴ ﺗ ﺍﻟﻜ ﻋﻠ ﻳﻚ ﻣ ﺍﻟﻠ ﺯﻝ ﺃ ﻭ
ﻣ ﻟﻌ ﺗ ﻛﻨ ﻣ ﺍﻟ ﻣ ﻛ ﻣ ﻋﻠ ﻭ ﺓ ﻣﻜ ﺣ
ﻩ ﺍﻟﻠ ﻓﻀ ﻟ ﻛﺎﻥ ﻭ

ﻋﻠ ﻳﻚ ﻋﻈ ﻳﻤ ﺍ

ይህም ጥበብ ክብራችን በውሥጡ ያለበትን መጽሐፍ ቁርአን ነው፤ ቁርአን

ጥበብ የተሞላ መጽሐፍ ነው፡- 10፥1 “አሊፍ ላም ራ ይህቺ *ጥበብ*

ከተመላው መጽሐፍ ከቁርኣን አንቀጾች ናት። ﺍﻟ ﺗﻠ ﺍﻳ ﻋ ﻟ ﺗ
ﻣ ﺍﻟﻜ ﺑ ﺗ ﺍﻟﻜ

30፥2 ይህች *ጥበብ* ከተመላው መጽሐፍ አንቀጾች ናት።ﻋ ﻟ ﺗ
ﺑ ﺗ ﺍﻟﻜ ﺗﻠ ﺍﻳ

ﻣ ﺍﻟﻜ ﺣ 36 ፥2 *ጥበብ* በተመላበት ቁርኣን እምላለሁ።ﻭ ﺍﻟ ﻗ ﺭ
ﻣ ﺍﻟﻜ ﺣ ﺍﻥ ﺀ

4,ያልተጠኑ የኢትዮጵያውያን ፍልስፍና

ሀገራችን ኢትዮጵያ ገና ያልተጠኑ የበርካታ ጥንታዊ ሥነጽሁፎች ባለቤት ናት፤ ማጥናት አቅቶን ሌሎች አጥንተው የቅጂ መብቱን ከመውሰዳቸውና የታሪክ ክፍትት ተፈጥሮ በመጪው ትውልድ ተወቃሾች ከመሆናችን በፊት የዘርፉ ምሁራን ጥናትና ምርምር በማካሄድ፣ ዩኒቨርስቲዎች ጉዳዩን የምርምር አቅጣጫቸው ውስጥ በማስገባት፣ ዜጎችም ጥንታዊ የጽሁፍ ሃብታችንን አስፈላጊነት ተገንዝበን ከዘራፊዎች በመጠበቅ ሃላፊነታችንን ልንወጣ ይገባል።
ኢትዮጵያ ዘመናትን ያስቆጠሩ ሥነቃላዊና የጽሁፍ ፍልስፍናዎች ባለቤት ናት። ከአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በፊት ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በተለየ መልኩ በርከት ያሉ የፍልስፍና ስራዎችን በመስራት በቀዳሚነት የምትጠቀሰው ኢትዮጵያ፤ በጥንታዊው የግእዝ ቋንቋ ከተጻፉት የፍልስፍና ስራዎቿ መካከል ከፊሎቹን በትውልድ ካናዳዊ፣ በምርጫ ደግሞ ኢትዮጵያዊ የሆነው ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ በመተርጎም፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲታወቁ ሲያደርግ፤ ሌሎች በርካታ በግዕዝና በአረብኛ ቋንቋዎች የተጻፉ የጽሁፍ ስራዎች በጥንታዊ ቤተእምነቶችና ቤተመዛግብት ውስጥ ተቀምጠው ክላውድ ሰምነርን የመሰሉ ፈላስፎችንና የጥንታዊ ጽሁፎች ተመራማሪዎችን (philologists) እይታ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ።
ፍልስፍና በጥቅሉ የተጻፉትንና በቃል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉትን የጋርዮሽ የማህበረሰብ ወጎች፣ ልማዶች፣ጥበቦች፣ የእውቀት ዘርፎችንና አስተሳሰቦችን፤ በጠባቡ አተያይ ደግሞ በግለሰብ ፈላስፋዎች በአንድ ዘመን ተሰርተው በጽሁፍ የተላለፉትን ስራዎች ብቻ የሚመለከት ነው። በቃል

ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍናዎች በተረትና ምሳሌ፣ በምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ በዘይቤዎች፣ በቅኔዎችና በወጎች ሊገለጡ ይችላሉ። ስለ ጾታ ልዩነት፣ እድሜ፣ ፖለቲካ፣ ስነምግባር እንዲሁም ስለ ህጻናትና አረጋውያን ያለውን ነባር ፍልስፍና ማህበረሰቡ ባሉት የሥነቃል መከወኛ መንገዶች ያቀርባል። ለዚህም ነው ምሳሌያዊ አነጋገሮች የረዥምና ውስብስብ ማሳመኛዎች አጭር መገለጫዎች ናቸው የሚባለው።

እነ ዶክተር ክላውድ ሰምነር እና ወርቅነህ ቀልቤሳ በሥነቃላዊ መንገድ የተላለፉትን የኢትዮጵያውያንን ፍልስፍና ከኦሮሞ ህዝብ ቋንቋና ባህል ውስጥ አውጥተው ያሳዩባቸውን ስራዎች በአብነት መጥቀስ ይቻላል። ቀደምት አባቶቻችን መላው አፍሪካ ባልሰለጠነበት ዘመን ቀድመው ባህላችንንና ታሪካችንን በድንጋይ ቀርጸውና በብራና ጽፈው ስላስተላለፉልን ኢትዮጵያ ከስነቃላዊ ፍልስፍና ባሻገር በጽሁፍ ፍልስፍናም ተጠቃሽ ስራዎች አሏት።

ምንም እንኳን በዘመናዊነት ስም ጥንታዊ ባህላችንንና ቋንቋችንን ረስተን የጽሁፍ ሃብታችንን ሳንመረምር፣ በርካታ ዘመናትን የራሳችንን ስናንቋሸሽ፣ የምዕራባውያንን ስናደንቅ ብናሳልፍም፣ ጉዳዩ ያብሰለሰላቸው በጣት የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንና በርካታ ምዕራባውን የቻሉትን ያህል ለማሰባሰብ፣ ለማጥናትና ለዓለም ለማስተዋወቅ ችለዋል።

በዚህ ረገድ እነ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ፣ ታደሰ ታምራትና ስርግው ሃብለሥላሴ ከሃገር ውስጥ እንዲሁም ፕሮፌሰር ፓኦሎ ማራሲኒ፣ አሌሳንድሮ ባውዚ፣ ሪቻርድ ፓንክረስትና ክላውድ ሰምነር ከውጪ ሃገር ቀዳሚ ተጠቃሾች

ናቸው። ካናዳዊው ክላውድ ሰምነር Classical Ethiopian Philosophy በተባለው መጽሐፉ ከግዕዝ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉሞ ያሳተማቸው የፍልስፍና ስራዎች- መጽሐፈ ፊሳልግዎስ፣ አንጋረ ፈላስፋ፣ የስክንድስ ህይወትና አባባሎቹ፣ ሀተታ ዘርዓያዕቆብ እና ሀተታ ወልደ ህይወት ናቸው። እነዚህ ስራዎች በተለይ አፍሪካውያን የጽሁፍ ፍልስፍና ስለሌላቸው ፍልስፍና በአፍሪካ ውስጥ የለም በሚል ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት ሲሞግቱ ለነበሩ ምዕራባውያን፤ የማያዳግም መልስ በመስጠት ለአፍሪካ የፍልስፍና ታሪክ ብርሃን የፈነጠቁ ናቸው።

የዛሬው ጽሁፌ ዓላማም እነዚህን የፍልስፍና ስራዎች በአጭሩ ማስተዋወቅ ይሆናል። የጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ፍልስፍና፤ የውጪ የጥበብ ስራዎች ውርስ ትርጉምና ወጥ (original) የፍልስፍና ስራዎች በመባል ይከፈላሉ። በኢትዮጵያ የሥነጽሁፍና ታሪክ ውስጥ በመጀመሪያው ክፍል እንደተጻፈ የሚነገርለት የመጀመሪያው የፍልስፍና የጽሁፍ ስራ መጽሐፈ ፊሳልግዎስ (physiologus) ይባላል። ይህ የፍልስፍና ስራ በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተጻፈ የሚነገርለትን የጥበብ ስራ ከግሪክ ወደ ግእዝ ቋንቋ በመተርጎም የተሰራ ሲሆን ትርጓሜውም ተራ ሳይሆን ከኢትዮጵያ የባህልና የቋንቋ አውድ ጋር በማዛመድ የተሰራ ነው። ፊሳልግዎስ በአምስተኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ወይም አጋማሽ አካባቢ ከፍተኛ የመጽሐፍ ክምችት በሚገኝበት ምናልባትም በግብጽ ሀገር በሚገኝ ገዳም ውስጥ በሚኖር ኢትዮጵያዊ ጸሐፊ እንደተጻፈ ይገመታል። ፈላስፋው ሰምነር የጥንታዊ ድርሳናት ተመራማሪው (philologist) ፍሪትዝ

ሆሜል (Hommel) በ1877 ዓ.ም በለንደን፣ ፓሪስና ቬና ቤተመዛግብት ውስጥ የሚገኙ የግእዝ ብራና ፊሳልግዎስ መጻህፍትን ከጀርመንኛ ትርጓሜው ጋር በማገናዘብ ካዘጋጀው የተስተካከለ ቅጽ (critical edition) ላይ የተረጎመው ሲሆን ከካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ የ1951 ጣልያንኛ ትርጉም ጋርም አመሳክሮታል። ፊሳልግዎስ ለመጽሐፉ ደራሲ የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ይህም እንስሳትን፣ ዕጽዋትናና የማዕድናትን ምንነት የሚገልጽና በተምሳሌት (symbolism) የሚያስቀምጥ ነው።

በኢትዮጵያ የስነጽሁፍ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ግምት በሚሰጠውና ሁለተኛው ክፍለ ዘመን በመባል በሚታወቀው የአጼ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግስት (1434-68) ፤ መጽሐፈ ፈላስፋና የስክንድስ ህይወትና አባባሎቹ የተባሉ ሁለት የፍልስፍና መጻህፍት ወደ ግእዝ ቋንቋ ተተርጉመዋል። ምናልባት እነዚህ ትርጉም ስራዎች እንዴት የኢትዮጵያ ፍልስፍና የሚል ስያሜ ሊሰጣቸው ቻለ የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ሰምነር እንደሚለው፤ ምንም እንኳ ስራዎቹ ትርጉም ቢሆኑም ኢትዮጵያውያን የራሳቸው የሆነ ወጥ የአተረጓጎም ስልት ስላላቸው ኢትዮጵያዊ አሻራ ይይዛሉ Ethiopians never translate literally: they adapt, modify, add, subtract. A translation therefore bears a typically Ethiopian stamp” (ኢትዮጵያውያን በትርጉም ሂደት ላይ ከራሳቸው ባህልና አውድ ጋር ለማዋሃድ ሆነ ብለው የመጨመር፣ የመቀነስና የማሻሻል ባህል ስላላቸውና ፍጹም ኢትዮጵያዊ አሻራ አንዲኖረው በማድረግ ስለሚተረጉሙ ነው።) መጽሐፈ ፍልስፍና፤ አንጋረ ፈላስፋ

ወይም የፈላስፎች አነጋገር በመባል የሚታወቅ ሲሆን ከ1510-1522 ዓ.ም አባ ሚካኤል በተባለ ኢትዮጵያዊ ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግእዝ የተተረጎመ ነው። መጽሐፉ መጀመሪያ በግሪክ እንደተጻፈና በ809 ዓ.ም አካባቢ ሁናይን ኢብን ኢስሐቅ በተባለ የሜሶፖታምያ ተወላጅ ወደ አረብኛ ቋንቋ የተተረጎመ ነው። መጽሐፈ ፈላስፋ በ1953 ዓ.ም በሊቀመዘምራን ዕቁበጊዮርጊስ አንጋረ ፈላስፋ በሚል ወደ አማርኛ ቋንቋ የተተረጎመ ሲሆን በውስጡም ከጠቢቡ ሂቃር ጥበብ ጀምሮ፤ የቅድመ ሶቅራጠስ የግሪክ ፈላስፎችን የሶቅራጠስን፣ የአሪስቶትልን (አሪስጣጣሊስ) በተለይ ደግሞ የፕሌቶንና (አፍላጦን) የፕሌቶን ተከታዮች አነጋገሮች አካቶ የያዘ የፍልስፍና ስራ ነው። ሦስተኛው የኢትዮጵያውያን የፍልስፍና መጽሐፍ የስክንድስ ህይወትና አባባሎቹ በሚል ርዕስ የተጻፈው ነው። በጀርመን ሀገር ከሚገኘው የግእዝ ብራና መጽሐፍ ላይ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ የተመለሰው ይህ መጽሐፍ፤ የሲግመንድ ፍሮይድ (Oedipus complex) ንድፈ ሃሳብ የተመሰረተበትን ታሪክ በጽሁፍ ይዘው ከተገኙት አምስት የዓለማችን ቋንቋዎች (ግሪክ፣ ላቲን፣ ሲራይክ፣ አረቢክ እና ግእዝ) መካከል አንዱ መሆኑን ይናገራል፤ ክላውድ ሰምነር። ከአረብኛ ቅጂ ላይ የተተረጎመው መጽሐፉ በሶስት ክፍሎች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው። የመጀመሪያው ክፍል የስክንድስን ህይወት ታሪክ፤ ሁለተኛው ክፍል ሃያ አምስት ጥያቄዎችና መልሶቻቸውን፤ እንዲሁም ሦስተኛው ክፍል ደግሞ አንድ መቶ ስምንት የፍልስፍና ጥያቄዎችንና ጠቢቡ ስክንድስ የሰጣቸውን ምላሾች ይዟል።

የመጨረሻዎቹ ሁለት የፍልስፍና መጻህፍት ከላይ ከቀረቡት ሦስት ስራዎች

በእጅጉ የተለዩ ናቸው። የኢትዮጵያ የጽሁፍ ፍልስፍና ከጥበብ (wisdom) ስራዎች ወደ አመክኖአዊ (rational)፤ ከውርስ ትርጉም ወደ ወጥ (original) ስራነት ለመሸጋገሩ ህያው ምስክሮች ናቸውና - የዘርዓያዕቆብ (ወርቅዬ) እና የተማሪው የወልደ ህይወት (ምትኩ) ሐተታዎች። በአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን (1599-1692) የህይወት ታሪኩንና የፍልስፍና ስራዉን ብራና ዳምጦ፣ ቀለም በጥብጦ፣ በመፃፍ ያቆየልን ኢትዮጵያዊ አመክኗዊ (rational) ፈላስፋ ዘርዓዕቆብ፤ በሃይማኖተኝነቱ፣ በስነጽሁፍ ስራዎቹና በብርቱ አስተዳደሩ ከሚታወቀው የአስራ አምስተኛው ክፍለ ዘመን (1434-68) ኢትዮጵያዊ ንጉስ አጼ ዘርዓያዕቆብ የተለየ መሆኑን ልብ ልንል ይገባል። ፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ፤ አጼ ዘርዓያዕቆብ ካለፈ ከ1.5 ምዕት ዓመት በኋላ በአጼ ሱስንዮስ የንግስና ዘመን እ.ኤ.አ በ1626ዓ.ም የተነሳ ፈላስፋ ሲሆን ሐተታ የተባለውን ፍልስፍና የሰራውም ለሁለት ዓመታት ያህል ለብቻው ዋሻ ውስጥ ተደብቆ በቆየባቸው ጊዜያት ነበር።የዘርዓ ያዕቆብና የተማሪው ወልደህይወት ሐተታዎች፤ በይዘታቸውም ሆነ በአቀራረባቸው ተመሳሳይነት አላቸው። ሐተታ የተባለው የፍልስፍና መንገድ አንድን ጉዳይ ደረጃ በደረጃ እየጠየቁ ጥልቅ ወደ ሆነ ምርምር የመግባትና በዚህም አንድ እውነተኛ እውቀት ላይ የመድረስ ሂደትን ያመለክታል።

ዘርዓያዕቆብ በጥንታዊት ኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት፤ በንባብ ቤት፣ በዜማ ቤትና በቅኔ/ሰዋስው ቤት ያለፈ ኢትዮጵያዊ ክርስቲያን ፈላስፋ ሲሆን እርሱ በነበረበት ዘመን የነበሩ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ፖለቲካዊና ሥነምግባራዊ

አስተሳሰቦችን በአመክኗዊ ሐተታ (rational inquiry) በመታገዝ ይመረምርና ይተች ነበር። የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና የፈጣሪ ህግን ከሰው ህግ፣ የተፈጥሮ ሥርዓትን ከሰብዓዊ ሥርዓት፤መለየትንና በአንድ አምላክ አማኞች ሃይማኖት ውስጥ የሚገኙ ተገቢ ያልሆኑ የሰው ሥርዓቶችን አስወግዶ በእውነተኛው የተፈጥሮ/የፈጣሪ ህግ ብቻ መመራት ላይ ያተኩራል። በተፈጥሮ ህግና በምክንያታዊነት መነጽር በመታገዝ ስለሃይማኖት መከፋፈል፣ስለሙሴና ነቢዩ መሀመድ ህጎች፣ ሐሰተኛ እምነትን ስለመለየት፣ ስለአምላክና ስለሰው ህግ፣ስለ እውነተኛ እውቀት ምንጭ እንዲሁም ስለጋብቻና ምንኩስና ተፈላስፏል። በአፍሪካ የጽሁፍ ፍልስፍና መገኘት የውስጥ እግር እሳት የሆነባቸው ምዕራባውያን፤ የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና የኢትዮጵያውን ስራ አይደለም ሲሉ ሞግተዋል።

ለምሳሌ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ ስራው የGiusto d’Urbino ነው ብሎ ነበር። ነገር ግን ክላውድ ሰምነር ለዚሁ ሙግት መልስ ለመስጠት በጻፈው Ethiopian Philosophy (Vol,II) መጽሐፍ ላይ ጊስቶ ዲ አርቢኖ ከጻፋቸው ደብዳቤዎችና ሌሎች ስራዎች፣ ሐተታው ከተጻፈበት የቅኔ ባህል፣ እንዲሁም በጉስቶ ትዕዛዝ ስለተገለበጠው ሐተታ ጸሐፊ የግዕዝ ቋንቋ እጥረት አንጻር የማያዳግም ምላሽ ከሰጠ በኋላ የሚከተለውን ድምዳሜ አስቀምጧል፤ MODERN PHILOSOPHY, in the sense of a personal rationalistic critical investigation, BEGAN IN ETHIOPIA with Zara’yaecob at the same time as in England and in France.” (በግለሰብ ፈላስፋ ደረጃ

የሚካሄድ ዘመናዊ የአመክንዮ ፍልስፍና በኢትዮጵያ ተጀምሯል፤ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ሀገር በተጀመረበት በተመሳሳይ ጊዜ እንደማለት) ዘመንፈስቅዱስ አብርሃ፤ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ጥበብ ለአሁኑ ትውልድ ለማሳወቅና ለወደፊቱ ለማስተላለፍ ከነበረው ምሁራዊ ሃላፊነት አንጻር ልዩ ልዩ የጥበብ ስራዎችን ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተርጉሞ በማሳተም ለንባብ አብቅቷል። ሐተታ ዘርዓያዕቆብ ወልደህይወትንም እ.ኤ.አ በ1955ዓ.ም በፈረንሳይ ሃገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ግእዝ ብራና መጽሐፍ ላይ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተርጉሞ አሳትሟል።

ፕሮፌሰር ቴዎድሮስ ኪሮስም፤ የፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነርን መንገድ ተከትሎ የዘርዓያዕቆብን ፍልስፍና ከፈረንሳዊው የአውሮፓ ዘመናዊ ፍልስፍና መስራች ሬኔ ዴካርት (Rene Descartes) ሥራ ጋር በማነጻጸር፣ ኢትዮጵያ በፍልስፍና ታሪክ ውስጥ የነበራትን ሚና ለተቀረው ዓለም አጉልቶ አሳይቷል። የዘርዓያዕቆብ ፍልስፍና ዛሬ ሊታወቅ የቻለው ካናዳዊ ዜግነት ባለው ሰምነር አማካኝነት ነው። የውጪ ሰዎች የኛን ጥንታዊ መጻህፍት ለማጥናት ይህን ያህል ከተጉ እኛ ኢትዮጵያውንማ ። ሀገራችን ኢትዮጵያ ገና ያልተጠኑ የበርካታ ጥንታዊ ሥነጽሁፎች ባለቤት ናት፤ ማጥናት አቅቶን ሌሎች አጥንተው የቅጂ መብቱን ከመውሰዳቸውና የታሪክ ክፍትት ተፈጥሮ በመጪው ትውልድ ተወቃሾች ከመሆናችን በፊት የዘርፉ ምሁራን ጥናትና ምርምር በማካሄድ፣ ዩኒቨርስቲዎች ጉዳዩን የምርምር አቅጣጫቸው ውስጥ በማስገባት፣ ዜጎችም ጥንታዊ የጽሁፍ ሃብታችንን አስፈላጊነት ተገንዝበን ከዘራፊዎች በመጠበቅ ሃላፊነታችንን

ልንወጣ ይገባል እላለሁ።

የፍልስፍና እይታ ክፍል 1 በዚህ ተጠናቋል። በክፍል 2 ላይ ስለ ፍልስፍና ብዙ ነገሮችን ጠለቅ ባለ ሁኔታ እንመለከታለን።

ከምንመለከታቸው ነገሮች 1,ታዋቂ ፈላስፎችና እይታዎቻቸው

2,የፍልስፍናን ምንነት ለማወቅ አንዳንድ ሰዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች

እና ብዙ ነገሮችን ዘርዘር ባለ ሁኔታ እናያለን።

ለማንኛውም አስተያየት በስልክ ቁጥር 0938713287 መስጠት ይቻላል።

ጸሀፊ ናርዶስ ለማ ገምጋሚት ቅድስት ለማ

Email-
fyodoredostovosky@gmail.com

የፍልስፍና እይታ ክፍል 2 ይቀጥላል